**መህሪባን አሊየቫ**
**የአዛርባጃን ሪፐብሊክ የመጀመሪያ ምክትል ፕሬዝዳንት**
**የተባበሩት መንግሥታት የኢኮኖሚ፤ የሳይንስ እና ባሕል ድርጅት (ዩኔስኮ) የበጎ ፈቃድ አምባሳደር**
**የሃይደር አሊየቭ ፋውንዴሽን ሊቀ-መንበር**



# ካራባኽ - ሙጋም ቤተ - ትምህርት




በተባበሩት መንግሥታት የኢኮኖሚ፤ የሳይንስ እና ባሕል ድርጅት (ዩኔስኮ)ውሳኔ መሰረት የአዛርባጃን ሙጋም የሰው ልጅ የማይዳሰሱ ቅርሶች ተብሎ ታውጇል። ሙጋም እንደ ህዝብ መሰረታዊ ባህላዊ እሴቶች ሥርዓት ዋነኛ ክፍል ተደርጎ በሚታይበት አዛርባጃን ይህ ውሳኔ በዘውጉ ግሩም ችሎታ ላላቸው እውቅና እንደመስጠት ብሎም ዓለም አቀፉን ህብረተሰብ ወደዚህ ልዩ ወደሆነው ቅርስ የመሳብ ፍላጎት ተደርጎ ይቆጠራል።

የዘመናት ታሪክ ያለው ከፍታ ላይ የደረሰው ተመራማሪዎች የምስራቅ ትንሳኤ ብለው በሚጠሩት ዘመን እና በግሪክ-ሮማ ቅርስ ላይ የተመሰረተው የአዛርባጃን ባህል ከስነ ጽሁፍ እስከ ኪነ-ህንጻ ድረስ በተለያዩ ዘርፎች ምርጥ ምርጥ ስራዎችን ለዓለም ባበረከተበት ወቅት ነው፡፡

በተደጋጋሚ/በተከታታይ ጊዜ እያደገ የመጣ ቢሆንም መሰረቱን እና ጠቀሜታው ግን እስካሁን ድረስ አልለቀቀም፡፡ **በአንድ በኩል ያለፈ ጊዜ ቅርስ በሌላ በኩል ደግሞ እጅግ ዘመናዊ ስነ-ጥበብ በመሆን የባሕል ብዝሃነት እንደያዘ ቀጥሏል። አስገዳጅ የሆኑት የ ህጎች ለመሻሻል እና ለፈጠራ እድገት እድልም ይሰጣሉ።**

እጅግ ልዩ የሆነው የሙጋም ባሕል ተዝቆ ከማያልቅ ፍልስፍናዊ፣ ሙዚቃዊ እና የስነ-ጽሁፋዊ መሰረቶች የተወለደ እና ያደገ ነው፡፡ አድማጮች የሙጋም ተጫዋቾችን ልክ ልዩ እንደሆኑ አስማታዊና ሚስጥርዊ ጥንታዊ ጥበብ ከትውልድ ትውልድ እንደተላለፈላቸው ባለሙያዎች ይቆጥሯቸዋል፡፡ ይህ እምነት አድማጮች ዘላለማዊ እውነት ጋር እንዲግናኙ እድል በመፍጠር የአእምሮ እፎይታ ይሰጣቸዋል፡፡

የዚህን የኪነ-ጥበብ ዘርፍ የህይወት ምንጭ በትክክል ለመግለጽ የሚችሉ የትምህርት መጽሃፍት አይገኙም፡፡ የሙጋም ተጫዋቾች ምስጢራዊ ከሆነ ማህበረሰብ የተገኙ ይመስል ይህን የሙጋም መኖሪያና ሁሌም አረንጓዴ የሆነውን የስነ-ቃል እና ሙዚቃ ዛፍ በሚገባ ማሳየት ይችላሉ። ልክ እንደ ሰው ሰራሽ ስነ-ጽሁፍ በምሳሌና ምስል ከተሞላው ከጥንታዊ የአዛርባጃን ስነ-ቃል የተመሰረተ ነው። ኤዞጳዊ ስልት ከሚስጥራዊ ትርጉም ጋር ይሰባጠራል። የእያንዳንዱ ስነቃላዊ መስመር አውዳዊ ትርጉም የሚገለጠው የምስራቅን ፍልስፍ እና የምልክትና ቅኔ ቋንቋ አጠቃቀምን ለሚያውቁ ሰዎች ብቻ ነው።

ከጥንት ጀምሮ የሙጋም ተጫዋቾች በጋዜል ጽሁፎች በስፋት ጥቅም ላይ እንደዋለው የመላመድ አይነት ወረት ያዳብራሉ። አንድም የሙጋም ተጫዋች የምን ያህል የጋዜል ገጣሚያን ስነ-ጽሁፎች እንደሚያውቅ ሊነግራችሁ አይችልም። በአንድ ጉዳይ ላይ ሃሳቡን መግለጽ ሲኖርበት ግን አግባብ ያላቸውን ጥቅሶች ማለት አይገደውም።



ለአዛርባጃን ሙዚቃ ቀማሪዎች የማይነጥፍ መነሻ የነበረና የሆነ ነው። በጥንታዊ ሙዚቃ መሰረት የተፈጠረው ሲምፎኒክ በተለያዩ ሃገራት ኦርኬስትራዎች በከፍተኛ ደረጃ ጥቅም ላይ ይውላል። በተመሳሳይ ለዘመናዊ ቀማሪዎች ወሰን የለሽ የአሰሳና ትርጓሜ ምንጭ ነው። ን በደንብ ለሚያውቁ ከራሱ ከ በእጅጉ ከሚርቁ የተለያዩ ቅንብሮች ውስጥ ሊያስገቡት ይችላሉ።

ያለመሳሪያም በመሳሪያ ታጅበው ለሚያቀርቡ ተጫዋቾች የታሰበ ሲሆን በመላ አዛርባጃን በስፋት ይታወቃል። በመሳሪያ የሚታገዙት የ ባንዶች የተለየ ቅንብር ሊኖራቸው ቢችልም ሁልጊዜ ለአጃቢ ብቻ ከሚቀርቡት ይበልጣሉ።

ባለመሳሪያው ዓይነተ ብዙ ቢሆንም እንደ ከፍታ የሚቆጠረው ግን የነጠላ ወይም ያለመሳሪያ የሚደረገው የሙጋም ጨዋታ ነው። አድማጭ የሱፊን ምስጢራዊነት በደንብ ሊሰማ እና "ከዋክብትን መጋለብ" የሚያስችል እና ቀማሪዎች የሙዚቃ ስንስል ምንነት ብለው እንደሚጠሩት አይነት ስሜት ሊሰጥ የሚችለው የነጠላ ጨዋታ ነው።

የሙጋም ዘፋኞች በአዛርባጃን በተለምዶ ካነንዴ (khanende) ተብለው ይታወቃሉ። ካነንዴ በአብዛኛው በሙዚቃ መሳሪያ ታጅቦ ይጫዎታል። ባህላዊ መሳሪያዎችን የሚጫዎተው የሙዚቀኞች ባንድ ከባለሦስት (ታር፣ ካማንቻ፣ እና ዴፍ) እስከ ሙሉ ኦርኬስትራ ድረስ ሊሆኑ ይችላሉ። **አዛርባጃን ውስጥ በርከት ያሉ የታወቁ የሙጋም ሙዚቃ ትምህርት ቤቶች አሉ። ምንም እንኳን ይህ የሙዚቃ ዘውግ በመላ ሃገሪቱ የተስፋፋ ቢሆንም የተለያዩ የሙጋም ትምህርት ቤቶች ያሉት ባኩ፣ ሸማካ፣ ጋንጃ፣ ናክሸቫ እና ሹሻ ናቸው። ካራባኽ የ ትምህርት ቤት (*Karabkh School of Mugham*) የሚባለውና በተለየ ሁኔታ በዋናነት የዳበረው በሹሻ ነው።**





የአዛርባጃን ለመጀመሪያ ጊዜ የተቀረጸው/የተቀዳው እ.ኤ.አ በ1902 ዓ.ም ነው። የሙጋምን ሙዚቃ በድምጽ በመቅረጽ ፈር ቀዳጅ የነበሩት የእንግሊዙ “ግራማፎን (Gramaphone)”፣ የጀርመኑ “ስፖርት ሪከርድ (Sport Record)”፣ እና የፈረንሳዩ “ፓት ሪከርድስ(Pate Records) ናቸው። እ.ኤ.አ በ1913 እነኝህ ድርጅቶች ወኪል ቢሮዎችን ሪጋ፣ ሞስኮ፣ ዋርሳው፣ ፒተርስበርግ፣ኬቭ፣ ቲብሊስ፣ እና ባኩ ውስጥ ከፈቱ። የአዛርባጃን በሩሲያውያኑ “ኮንሰርት ሪከርድ(Concert Record)”፣ ሞናርክ ሪከርድ



(Monarch Record)፣ ኤክስራፎን (Extraphone” እና “ግራማፎን ሪከርድ (Gramaphone Record)”፣ በሃንጋሪያዊያኑ “ፕሪሚየር ሪከርድ (Premier Record)” ድርጅቶች ተቀርጸዋል።

በሶቪየት ጊዜም በአፕረሌቭካ (Aprelevka) እና ኖጊን (Nogin) በተባሉ ድርጅቶች በርከት ያሉ ጠቃሚ ቀረጻዎች ተደርገዋል።

ከእነኝህ አብዛኞቹ ቅጆች በአዛርባጃን የመንግስት የድምጽ ቅጅ ማህደር (Azerbaijan State Archives of Audio Records) ይገኛሉ። ጥቂቶች በአዛርባጃን የመንግስት የሚዚቃ ባህል ሙዚየም ይጠበቃሉ። አንዳንድ የአዛርባጃን ጥንታው ቅጅዎች ደግሞ በብሪታንያ ላይብራሪ የድምጽ ማህደር ውስጥ ተከማችተዋል። በአዛርባጃን ጥንታዊ ቅጅዎችን ለመመለስ ብዙ ጥረት ተደርጓል። ለምሳሌ የ20ኛው ክ/ዘ መጀመሪያ ቅጅዎች ወደ ዲጂታል ፎርማት ተቀይረዋል። በአንድ ቅጅ ብቻ በመቀዳታቸው እና ለስርጭት የታሰቡ ስላልነበሩ ከዚህ በፊት ተሰራጭተው አያውቁም።

በአንደኛው የዓለም ጦርነት አማካይነት የተከሰተው የፖለቲካ እልቂት፣ የሩሲያ ግዛት መፈረካከስ እና የሶቪየት ህብረት መመስረት ለ የሙዚቃ ዘውግም ከፍተኛ ቀውስ ፈጠረበት። በሶቪየት ርዕዮት ጡረታ እንደወጣ እና ለሰራተኛው ማህበረሰብ ባዳ እንደሆነ ተደርጎ ተቆጠረ።

የሙጋም ጨዋታ ዋና መሳሪያ የሆነው ታር እንኳን ከጥቃት ማምለጥ አልቻለም ነበር። በድብቅ ሲተገበር የነበረው የኋላ ኋላ ይፋዊ ባህል በመሆን ወደቀደመ ህይወቱ ተመልሷል። ሆኖም ግን የመጀመሪያዎቹ ከፍተኛ ጥራት ያላቸው የካራባኽ ትምህርት ቤት የ የስቱዲዮ ቅጅዎች እ.ኤ.አ. ከ1930-50ዎቹ ነው የተሰሩት። እነኝህ ቅጅዎች የእነ ካን ሹሺንስኪን፣ ዙልፊ አዲገዛሎቭን፣ ሙታሊም ሙታሊሞቭን፣ ያጉብ ማማዶቭን፣ ኢስላም ዛየቭን፣ አሪፍ ባባየቭን፣ ሙርሸድ ማማዶቭን፣ ጋዲር ሩስታሞቭን፣ ሱለይማን አብዱላየቭን እና የሌሎችንም ድምጾች ይያዙ ናቸው። በመጨረሻም በ20ኛው ክ/ዘ የሶስተኛው ቡድን ተጫዋቾች እውቅናን አገኙ። የዚህ ዘመን ተወካዮች ደግሞ እነ ቫሂድ አብዱላየቭ፣ ሳካቤት ማማዶቭ፣ ዛሂድ ጉሊየቭ፣ጋራካን ቤቡዶቭ፣ ማንሱም ኢብራሞቭ፣ ሳቢር አብዱላየቭ እና ፌሩዝ ማመዶቭ የተባሉት ካናንዴዎች ናቸው።

ለአንድ ታላቅ ተሰጥኦ መወለድ ሰዎች ለዘመናት ዝግጅት ማድረግ አለባቸው ይባላል።አንድ ባለተሰጥኦ ሲወለድ የእሹሩሩ እንጉርጉሮዎን ሊሰማ ይገባል፣ ክፉና በጎ እንዲለይ የሚረዱ አፈታሪኮች ሊነገሩት ግድ ይላል፣ የቅድመ አያቶችን ቅርሶች የሚያወዳድሱ ዘፈኖችም ማድመጥ አለበት። አንድ ነገር ግልጽ ነው፤ ሰዎች እና አካባቢ ባለ ተሰጥኦን ለመቀበል ዝግጁ ካልሆኑ ያ ሰው ሳይታወቅ ብሎም ራሱን ሳያውቅ ሊያልፍ ይችላል። ይህን ስንመለከት በቀላሉ ሊቀበላቸው የሚችል ማህበረሰብ ባለበት ጊዜና ቦታ በመወለዳቸው የካራባኽ ካናንዴዎች እድለኞች ያስብላቸዋል።

በዋናነት ካራባኽ ውስጥ መወለዳቸው እጣ ፋንታቸውን ይወስነዋል። ሁሉም ሰው ማዜም እና አሪፍ ድምጽን እና የሙዚቃ ተሰጥኦን ማድነቅ በሚችልበት ቦታ ተወልደዋልና። በላይኛውም ሆነ በታችኛው የሃገሪቱ ክፍል (ሹሻ እና አግዳም) ይወለድ ሁሉም የአዛርባጃን ሰው የሙጋም ሙዚቃ አዋቂ ሲሆን ማንኛውንም አይነት የባህል ቅኝት ይጫዎታል። የሰውን ነፍስያ ይቀርጻል ተብሎም ይታመናል። ይህ ነገር ካራባኽ ውስጥ እርስ በእርሱ የተሳሰረ ነው። ተፈጥሮ ሙዚቃን ጨምሮ ማንኛውንም አይነት ስነ-ውበታዊ ቁሶች በቀላሉ የመቀበል ዝንባሌ ያላቸውን ነፍሶች ቀርጿል። የእነዚህ ቦታ ውበት እና መስማማት በሁሉም በልዩ ሁኔታ በዳበረው የካራባኽ ተጫዋጮች የሙዚቃ ባህል ላይ ተንጸባርቀዋል።

ብዙዎቹ የካራባኽ ካናንዴዎች የተወለዱት ሹሻ ውስጥ ነው። የሹሻ ገጽታ፣ የማይታበለው ምሽግነት እና መንፈሳዊ ግንብነት ምስልነቷ እና የአዛርባጃናዊያን የባህላዊ አምልኮ ቦታ ሁሌም የስራዎቻቸው ዋና ጭብጥ ይሆናሉ።

እያንዳንዱ የሹሻ ተወላጅ ታሪኩን በሚገባ ያውቃል። ይህ እውቀት ግን ከታሪክ ድርሳናት ብቻ የተገኘ አይደለም። ብዙዎቹ “የካራባኽ ታሪኮች (The Karabakhname)” በእጅ በተጻፉ መጽሃፍት ብቻ የሚታዩ አይደሉም። ያለፈ እና የአሁኑ ህይወታቸው ዋነኛ ክፍልም ናቸው እንጅ። በእነሱ ውስጥ የተገለጹ ብዙ የታሪክ ክፍሎች ከትውልድ ትውልድ እየተላለፉ ተደጋግመው ተነግረዋል። በመሆኑም የክስተቶች ትንንሽ ዝርዝሮች እንኳን በአግባቡ ተጠብቀዋል። የካራባኽ ታሪኮች የእለተለት ህይወትነ፣ ኪነ-ህንጻን፣ ባለፉና አሁንም ባሉ ታሪኮች በካከል ባለ የእርስ በርስ ተደጋግፎ ላይ በተመሰረት እውነታን የሚያንጸባርቁ ህያው ታሪኮች ናቸው። የእነዚህ ቦታዎች ተፈጥሮ እና ታሪክ ከዋናዋናዎቹ የካራባኽ ትምህርት ቤት ጭብጦች መሃል የሆነውን “ካራባኽ”ን ፈጠረ። በስፋት የሚታዎቀው “ካራባኽ ሺኬስተሲ” አሁን ድረስ ለካራባኽ ዘፋኞች የጉብኝት ካርዳቸው ነው።

ሹሻ የሩሲያው ባለቅኔ የሰኒን “ባለቅኔ ካልሆንክ ከሺራዝ አይደለህም፤ ሙዚቀኛ ካልሆንክ ከሹሻ አይደለህም” ያለውን በማሰብ ራሳቸውን ሹሺኒስኪ በሚል የቅጽል ስም የሚጠሩ ብዙ ሙዚቀኞችን ለዓለም አበርክታለች። ሺሻ ብዙ አስገራሚ ዘፋኞችን ፣ አቀናባሪዎችን እና በአንድ ሙጽሃፍ ሙሉ ተዘርዝረው የማያልቁ የፐርፎርሚንግ አርት ባለሙያዎችን ለዓለም አበርክታለች።

ሹሻ ሁሌም የምስራቋ የሙዚቃ ከተማ ተብላ ትወደሳለች። ሰዎች ሙዚቃን ለመስማትም ሆነ ለመማር ከሁሉም ቦታዎች ወደዚህ ይመጣሉ። ሆኖም ግን ከተማዋ የምትታወቀው በሙዚቀኞቿ ብቻ አልነበረም። የሹሻ ክስተት በልዩ ተፈጥሯዊ ሁነቶች እና የአካባቢው ሰዎች ድርጊቶች ጥምርታ ይወከላል። በከተማዋ የተለያየ አስተዳደግ ያላቸው በጣም ብዙ አስደናቂ ሰዎች የተወለዱ ሲሆን እስካሁን ራሳቸው በሰሯቸው የሙዚቃ መሳሪያዎች፣ በገነቧቸው አዳራሾች፣ በጻፏቸው ቅኔዎች አማካይነት ታይቶ የማያውቅ የሙዚቃ ስራዎችን ሰርተዋል። የከተማዋ አካባቢ ስለካውካሰስ ጉዞ በሚያትተው የአሌክሳንደር ዱማ መጽሃፍ ውስጥ ተንጸባርቋል። መጽሃፉ ከካራባኽ የፈለቀችው ገጣሚ ናታቫን በአስደናቂ አገላለጽ ያቀርባታል።

ንጹህና እና የጠሩ ምንጮች ለሹሻ የተለየ ሞገስ አሰጥተዋታል። ከሁሉም በላይ እውቅ የሆነው “ኢሳ ቡላግ” በብዙዎች ዘንድ የሹሻ ምልክት ተደርጎ ይቆጠራል። ወደጠፈር የሚጠቁሙ የሚመስሉ ተራሮቿ፣ አስደናቂውን










አምባ በመከበብ ልዩ የሆነ የቤት-ውጭ የሙዚቃ አዳራሽ ከማይታመን አኮስቲክ ጋር ይፈጥራሉ። ጂዲር ዱዙ አምባ ብዙ ባለዝና ዘፋኞችን በሚገባ አስተናግዷል። ከአይን የማይሰወሩት የሹሻ ወጣት ወንዶች ከዚህ የተፈጥሮ ተዓምር ጋር ተጫውተዋል።

እኤአ በ1987 ዓም የካሪቡልቡል ዓለም አቀፍ የ ፌስቲቫል ተካሂዶ ነበር። ፌስቲቫሉ የተሰየመው በአካባቢው ባሉ ተራሮች በምትበቅል አበባ ስም ነበር። በፌስቲቫሉ ምን ዓይነት ህብር ያላቸው ወጣት ባለተሰጥኦ አሳየ መሰላችሁ!! እ.ኤ.አ በ1991 ዓ.ም የሺሻ በወራሪ አርሜኒያ መያዝ እነኝህን ከዋክብት ለስደት ዳረጋቸው። በአሁኑ ሰዓት በስደተኛ ካምፖች ውስጥ ሆነው በሚያሳዝን ሁኔታ ከሙዚቃ ተገልለው ይኖራሉ። “እኛ የተራራ ሰዎች በሸለቆ ውስጥ መዝፈንም ሆነ መኖር አንችልም። ነፍሶቻችን በዚያ በሹሻ ናቸው። የጠሩ ተራራ ላይ ምንጮች እና ንጹህ የተራራ ላይ አየር በሌሉበት፣ ያለ ጂዲር ዱዙ አምባ ወፎች ዝማሬ እንዴትስ ብለን ልናቀነቅን እንችላለን።” ለዚህ ጥያቄ መልስ ሊኖር ይችላል? አንድ ሰው ይህን ህጻናት ዓለምን የሚያዩበትን ጥልቅ ስሜት ሲያይ በተስፋቢስነት ከመሸማቀቅ በቀር ምንም ማድረግ አይቻልም።

ባልተጻፉ ህጎች መሰረት በርከት ያሉ የሙዚቃ ስብስብ መደቦች አሉ። የመጀመሪያው መደብ የመጅሊሶች ሲሆን የሙዚቃ ልሂቃን የሚካተቱበት ነው። በተለይም ቀደም ብለው ተሰምተው በማያውቁ ግጥሞች ተመስርተው የተሰሩ ሙዚቃዎች ይ አድናቆት ይቸራቸዋል። ነገር ግን ጥራቱን እስከጠበቀ ደረስ ድምጻዊው ግጥሙን ከቆዩ መዛግብትም ሆነ ከዘመናዊ ምንጭ ያገኘው ቢሆንም ችግር የለውም፡፡ ለጭፈራ የሚሆኑ ጥዑም ዜማዎች በእንዲህ ዓይነት ዝግጅቶች ላይ የማይሰሙ ሲሆን ሙጋም ግን ደመቅ ይላል፡፡ ደረጃቸው ዝቅ ባሉ መጅሊሶች ላይ





የሚጋበዙት በሙያቸው እና ክህሎታቸው አነስ ያሉ ድምጻውያን ናቸው፡፡ ሙጋም እዚያም የሚደመጥ ሲሆን ከሁለት ሰዓታት በኋላ የሕዝብ ዜማ ተከፍቶ ታዳሚውም እንዲጨፍር ይፈቀድለታል፡፡ ቀደም ሲል ካልነው ዝቅ ያለ ደረጃ ያላቸው መጅሊሶች ደግሞ መዝናናት የሚፈልጉትን ያገናኛሉ፡፡ በእንዲህ ዓይነቶቹ ዝግጅቶች ላይ ጠንከር ያለ መልዕክት ያዘሉ ዜማዎች የማይሰሙ ሲሆኑ ካኔንዴዎች ከክብራቸው አንጻር አይመጥኑንም በሚል በእንዲህ ዓይነት ዝግጅቶች ላይ አይታደሙም፡፡ ከላይ ያነሳናቸው ፍረጃዎች ምንም እንኳ በቅድመ-ሁኔታዎች ላይ የተመሠረቱ ይሁኑ እንጂ ትልልቅ ደረጃ ያላቸው ሙዚቀኞች ያንን ደረጃቸውን ጠብቀው እንዲቆዩ አስችለዋል፡፡ ይህ በአድማጮችም ዘንድ የሆነ ነገር ነው፡፡ የትልቅ ጥበብ ሙያ ባለቤቶች በሙጋም ላይ መታደም የሕዝብ ዜማዎችን መሠረት ያደረገው ጥበብ በዕድገት ጎዳና እንዲጓዝ ትልቅ አስተዋፆ አድርጓል፡፡ እንደ ፀሐፊ አብዱራሒም ሐግቬርዲዬቭ ከሆነ በ 19ኛው መቶ ክፍለ-ዘመን ሁለተኛው አጋማሽ ላይ በባኩ፣ ሸማካ፣ አሽካባድ፣ ተኼራንም ሆነ ኢስታንቡል ከምናገኛቸው ምንም ዓይነት አርቲስቶች የተወሰኑት በእርግጠኝነት መሠረታቸው ከሹሻ ነበረ፡፡ እንዲህ ዓይነት መሠረት ያላቸው ሙዚቀኞች በምሥራቁ ዓለም የነበረውን የሙዚቃ ፋሽን በመቅረጽ ቀዳሚ ሚና የነበራቸው ሲሆን ታለንት እና ድምጻቸውን ማስገምገም ይፈልጉ የነበሩ ሰዎች ሁሌም ወደ ሹሻ ነበር ጉዟቸው፡፡ ከዓመታት በኃላ ዕውቅናን ያገኙ ካኔንዴዎች ሲሆኑ ከሐጂ ሁሴን፣ ሳዲቅጃን፣ ሚርዛ ሙክታር፣ ጀበር ጋሪያጂዮግሉ ወይንም ከሌሎች የካራባኽክ ሙጋም ጠቢባን ስለተሰጣቸው ፈተናዎች በኩራት ያወራሉ፡፡ በአዘርባጃን ለመጀመሪያ ጊዜ የነዳጅ ዘይት ሲገኝ በሙጋም ዕድገት ላይ የራሱን አሻራ አሳርፏል፡፡ በባኩ የነዳጅ ዘይት አምራቾች የተቋቋሙት የምሥራቅ ፓርቲዎች ትልቅ ስኬትን አግኝተዋል፡፡ የመጀመሪያው በሹሻ ቴያትር ነበር የተካሄደው፡፡ እነዚህ የምሥራቅ ፓርቲዎች ነበሩ የሙጋም ባለሙያዎች በሕዝብ ፊት ኮንሰርት እንዲያቀርቡ ያደረጉት፡፡ በ 20ኛው መቶ ክፍለ-ዘመን ላይ የካርባካ የሙጋም ት/ቤት ለሙዚቃው ዓለም እጅግ ተስፋ የሚጣልባቸውን ክዋክብት አበረከተ፡፡ የናጎርኖ-ካርባካ ጦርነት የካንዴኔን ዝግጅት አቋረጠው፡፡ ጠመንጃ ተናጋሪው ሲሆን ሀሳብ ዝም ይላል የሚል አባባል አለ፡፡ የካርባካ ካንዴኔዎች ዝም አላሉም፣ ዘፍነዋል፣፡ ሆኖም ስለ ስቃይ፣ ሀዘን እና እንግልት ነው የዘፈኑት፡፡ ታላቁ ጀበር ጋሪያጂዮግሉ እንዳሉት፣ *ገነት ገብቼም ቢሆን ኖሮ ያለ ካርባካ ሕይወቴ ከንቱ ናት*፡፡ በዚህች በፍጥነት ወደ አንድ መንደርነት እየመጣች በምትገኝ ዓለም በርካታ ነገሮች በለውጥ ላይ ይገኛሉ፡፡ የሰዎች ትራፊክ ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ መልኩ መኖሩ፣ መረጃ በአጭር ጊዜ ውስጥ ፈጥኖ መድረስ መቻሉ፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች የዓለምን ገጽታ መቀየራቸው-- ይህ ሁሉ እየተካሄደ ያለው እንደ ሽብርተኝነት እና የተፈጥሮ ጥፋት ያሉ አደጋዎች በተደቀኑበት ወቅት ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት ከባባድ አደጋዎች በተደቀኑበት ዓለም ደግሞ የሰው ልጅ የስንዴን ያህል ያንሳል፡፡ የሰው ልጅ ያጣውን ያንን መጣጣም እና መስማማት የነበረበት ሕይወት የግሎባላይዜሽንም ሆነ ፀረ-ግሎባላይዜሽን አራማጆች ሊመልሱለት አልቻሉም፡፡ በመሆኑም ይህ ዘመን ለወደፊቱ እና ከባሕላችን ጋር በተጣጣመ እና በተዛመደ መልኩ ለምናካሂደው ዕድገት እና ልማት መሠረት የምንጥልበት ነው፡፡ የባሕል ብዝሀነት እና ባሕል የሚከበርባት እና የሚጠበቅባት ዓለምን መፍጠር የምንችለው የእያንዳንዱን ሥልጣኔ እና ሕዝብ ባሕል ብሎም ወግ በመጠበቅ ብቻ ነው፡፡ የተባበሩት መንግሥታት የኢኮኖሚ፣ የሳይንስ እና ባሕል ድርጅት (ዩኔስኮ) የማይዳሰሱ ቅርሶችን ለመጠበቅ ያወጣው ስምምነት ዓላማም ይኸው ነው።